# የባሕር-በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ <u>ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ፤</u>

*የግል አስተያየት፡- አያል ሰው ደሴ*　　　*ሰኔ፡ ሁለት-ሽህ-ሦስት ዓ/ም - ክፍል አንድ*

ብዙ ወገኖች የባሕር በር ጥያቄን የንግድ ሸቀጣ-ሸቀጥ ወደ-አገር ውስጥ ማስገቢያና ከአገር ወደ-ውጭ ማስተላለፊያ በመሆኑ ረገድ ከአለው መደበኛ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ጎን ብቻ እንደሚያዩት የታወቀው ነው:: አዎን፣ ልክ ነው፤ ማንኛውም አገር የባሕር በር ሲኖረው እነዚኽን ጥቅሞች መስጠቱ የታወቀም፣ የተረጋገጠም ሃቅ ነው:: ሆኖም ያ አንዱ የባሕር በር ጠቃሚ ጎን ሲሆን፤ ከዚኽ ግልጥ ጠቀሜታ የበለጠ ሌላ አስፈላጊነት እንዳለው ደግሞ መገንዘቡ ሊታወቅ ይገባል እላለሁ:: ያ <u>ሌላው የአስፈላጊነት ጎን የአንድን አገር አንድነት፣ ሰላም፣ መረጋጋት፣ ዘላቂነትና ተከታታይነት ያለው አስተማማኝ የምጣኔ ሃብት እድገትና ብልፅግና የማስገኘትንና እንደ-አገር ኅልውናን እና እንደ-ሕዝብም ሉዓላዊነትንና ክብርን የሚያኽሉ ከባድ ከባድ እሴቶችን የሚወስን ቁልፍ ሚና</u> ይሆናል:: የዚኽ ጽሑፍ ዓላማም ይኽንኑ በአጭሩ ለመዳደስ ነው::

በኢትዮጵያ የቀደምት ሥልጣኔ መሠረት ከሚባሉት ሥፍራዎች (አካባቢዎች) አንዷ የሆነችው የጥንቷ ምድረ-ባሕር/ሪ የአሁኗ ኤርትራ እና ለአገሪቱ አንድነትና ለማንነታቸው ባሕር ተሻግረው ወረራ ከቃጡና ከአካሄዱ ባዕዳን ጋር ከዘመን ዘመን እየተናነቁና ክቡር ሕይዎታቸውን እየገበሩ የኖሩ ወገኖቻችን ምንም ዓይነት ሕጋዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረት በሌለው ኢ-ፍትኃዊ ብይን የዛሬ ሃያ ዓመታት እንዲለዩና አገሪቱ ከሁለት እንድትቆረስ መደረጉ ይታወቃል:: ኢትዮጵያውያን ያንን በማንም "የሽግግር መንግሥት" ሊወሰድ የማይችል ብቻ አይደለም ጨርሶ የማይታሰብ ዕብሪታዊ ፍርደ-ገምድል እርምጃ በማይሽር ቁጭት የተመለከቱት ጉዳዩን ከስሜታዊነት በወጣና በረጋ መንፈስ ማየት የሚያስችል ፋታ ሣይኖር፣ ሕዝቡ ሣይመክርበት በዘፈቀደ አካላቸው ተቆርሶ በመሄዱ የሕዝቡን ማኅበራዊና ታሪካዊ ትሥሥር ገመድ የሚበጥስ፣ ለአጠቃላይ የአገሪቱ ሕዝብም ሆነ ለኤርትራውያን ወገኖቹ ምንም ዓይነት ዘለቄታዊነት ያለው ጠቀሜታ እንደማይኖረውና በሁለቱም በኩል የሚያስከትለውን ውስብስብ መዘዝ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው::

በመሆኑም ጠባብ መሠረት ባላቸውና የልዩነትም ሆነ የቅራኔ መፍቻ መንገድ አመፅ/ኃይል ብቻ አድርገው በወሰዱ ሁለት ታጣቂ የአመፅ ድርጅቶች - ሕወሓት እና ሕግኃኤ (ሸዓብያ) - የተወሰደ ያ ግብታዊ ብይን ከታሪክ፣ ከማኅበረሰብ ትሥሥር፣ ከሕዝብ መብትም ሆነ ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ ያልተቃኘና በወደ-ፊት ትውልዶች ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ ጨርሶ ያላገናዘበ፣ ኃላፊነት የጎደለውና በቅርቡ አጮልቆ ያየ እኩይ ሴራ ነው ማለት ይቻላል::

ጉዳዩን ይበልጥ አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ ኩሩውን የአፋር ብሔረሰብ ከሁለት መክፈሉና እነኚኽን አገር-ወዳድ ዜጎች ተፈጥሮ ካስተሣሰራቸው ቀይ ባሕር የባለቤትነት መብት መንቀሉ ነው:: እንደሚታወቀው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ከወሰዷቸው እጅግ አከራካሪ፣ አፍራሽና ጠንቀኛ ብሔራዊ ጥቅምን የተፃረሩ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ይኽ በብዙ መስዋዕትነት የተገኘ የአገርን አንድነት ያናጋና አገሪቱን የባሕር በር-አልባ እንድትቀር ያደረገው በዋናነት የሚጠቀስ ነው ማለት እደፍራለሁ::

እኒኽ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የውሳኔአቸውን "ትክክለኛነት" ለማሣመን አንድም *"የኤርትራ ሕዝብ 'እራሴን ልቻል፣ ልገንጠል' የሚል ቁርጠኝነቱን በሰጠው ሕዝበ-ውሳኔ አረጋግጧል:: ያም ስለ-ሆነ በውሳኔው መሠረት ኤርትራ ስትገነጠል /"ነፃ ስትወጣ"/ ኤርትራውያን የእኛ ነው ይገባናል የሚሉትን የአገር ክፍል መውሰዳቸው የግድ ነው"፣ ... " የኤርትራ ሕዝብ ይኽን እራሱን የመቻል ፍላጎቱን ደግሞ አስቀድሞ በመሬት ላይ በሚታይ ወታደራዊ ፍልሚያ እውን ስላደረገው እኛ እንደገና አዲስ የጦርነት ዙር ከፍተን ልናስቆም አንችልም"..." ሸቀጦች ለማስገባትና ለማስወጣትም ይኹን ለንግድ ልውውጥ ኢትዮጵያ የኤርትራን ወደቦች በስምምነት መጠቀም ስለምትችል እራሷ በባለቤትነት የምታዝበትና የምትቆጣጠረው ወደብ አያስፈልጋትም፣..ወዘተ.."* የሚል ነበር:: በእነሱ ስሌት እንግዲኽ

“.. ኤርትራውያን የእኛ ነው ይገባናል የሚሉትን..” ሲሉ ባዕዳን ቅኝ ገዝዎች በጉልበታቸው ከልለውት የነበረውን ማለታቸው እንደሆነ ደግሞ ግልጥ ነው፡፡

ያ የመከራከሪያ ነጥብ ግን፤

- የጣልያን ተስፋፊ ወራሪዎች በ፲፱፻፴፫ (1933) ዓ/ም ተከለለ” የተባለውን “ወሰን” በጉልበታቸው ጥሰው ኢትዮጵያን ሲወርሩ፣
- አገር-ወዳዱ የኤርትራ ሕዝብ በተባበሩት መንግሥታት የክትትልና አጣሪ ቡድኖች አማካይነት ለቀረቡለት ተደጋጋሚ ጥያቄዎች “ኢትዮጵያ ወይ ሞት” የሚል መፈክራቸውን አንግበው ፍላጎታቸውና ትግላቸው “ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ መቀላልቀል” ስለሆነ ይኸ ታውቆላቸው ያለ-ምንም ቅድመ-ሁኔታና በረባ-ባልረባ ምክንያት ሣይጓተት ሙሉ ፍላጎታቸውና የፈረጠመ ውሳኔኣቸው ተፈጻሚ እንዲሆንላቸው ባደረጉት ትግል በፌደሬሽን ስም ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ጋር በጊዜው በነበረው አንድ የዘውድ ሥርዓት ሥር ሲጠቃለሉ (ሲተዳደሩ) እና አንድ አገር ሆነው ሲቆጠሩ፣
- ያንን ተከትሎም በቅድሚያ በአፄ ኃይለ-ሥላሴ ከዚያም በደርግ ጊዜ እንደ-ማንኛውም ሉዓላዊ አገር ኢትዮጵያም የውስጥ አስተዳደሯን በአመቻች ማደላደል መብቷ በመሆኑ በዚኽ ረገድ በወቅቱ መንግሥቶች በተወሰዱ እርምጃዎች የአሰብ ወደብን ይዞ ያለው አብዛኛው የአፋር ብሔረሰብ ክፍል በአውራጃ (አውሣ) ተደራጅቶ በወሎ ክፍለ-አገር ሥር መሆኑ፣ ቆይቶም የራስ-ገዝ እንዲሆን መደረጉ፣ ወዘተ.. ያ የተባለው የባዕዳን 'የወሰን አከላለል' እንደተሻረ ግልጥ ሊሆን ይገባል፡፡

ስለ-ሆነም ኤርትራ “ነፃ ትውጣ” ከተባለና ያን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ታሪካዊ መሠረትነት፣ ሕጋዊነት እና የሕዝብ ይሁንታን የመሣሰሉ ሁኔታዎች ከተሟሉ “ይገባናል” ሊሉ የሚችሉት ጥያቄውን ባቀረቡበት ወቅት ኤርትራ በተባለው ክፍል ሥር ያለውን ይዞታ ብቻ ይሆናል እንጂ በተደጋጋሚ የተሻሩ “ወሰኖችን” ሊያጣቅስ አይችልም፡፡

ምንም እንኳን የኢትዮ-ኤርትራ ግንኙነት የቅን-ገኝና ተገዢ ግንኙነት አለመሆኑ ግልጥ ቢሆንም፤ እንደዚያ ስሌት ከሆነ የአፍሪቃ አገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነፃነታቸውን ሲያገኙ የያዙትን ይዞታ ሣይሆን ቀደምት የነበሯቸውን ይዞታዎች ይገባኛል ማለት በቻሉ ነበር፡፡ ያ ደግሞ ትርምስምሱ የወጣ ሁኔታን ሊያስከትል መቻሉ አይቀሬ መሆኑ ግልጥ ስለ-ነበር ነው አገሮቹ ነፃታቸውን ሲያውጁ በዚያኑ ጊዜ የነበራቸውን ወሰን ይዘው የቀጠሉት፡፡ በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር <u>መልሣ እንድትቀላቀል</u> በተደረገው ጊዜ-የፈጀ ክርክር ላይ የተነሱ ነጥቦችን ዞር ብሎ ማስታወሱም ተገቢ ይሆናል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ ከጥንታዊት አካሏ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን እንድትተሣሰር ለወሰደው ውሳኔ በማሣመኛ ነጥብነት ገዥነት የነበረው የኤርትራ ሕዝብ ካደረገው ያላሰለሰ ትግልና ካሣየው ነፃ ፍላጎት በተጨማሪ አንዱ የማያወላዳ ግንዛቤ ታሪክን ያጣቀሰና ኢትዮጵያ የባሕር በር <u>ሊኖራት እንደሚገባ</u> የታመነበት ጉዳይ በመሆኑ ነበር ፡፡ በዚያ የክርክር ሂደት አጠቃላይ ኤርትራ ወደ-ኢትዮጵያ ትመለስ አትመለስ የሚል እንጅ ከመጀመሪያው ጀምሮ የአሰብ ወደብ ያለ-ጥያቄ የኢትዮጵያ አካል በመሆኑ ላይ ብዙ ጥያቄ ያልቀረበበትና አሣማኝ ተቃውሞ ያልተሰማበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የሆነ-ሆኖ የሕወሓት መሪዎች አገሪቱን ወደብ-አልባ ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ሲነሣ የቆየውና አሁንም ሣይበርድ የቀጠለው ጥያቄ ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሷ ልጆች የተነፈገችው ያ የባሕር በር ባለቤትነት ጉዳይ አግባባዊ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል የሚል ነው፡፡

ከንጉሡ ጀምሮ ለአገራቸው ክብርና ታላቅነት በጎ የሚያስቡና ይኽንኑ እውን ለማድረግና ለማረጋገጥ ያለ-የሌለ ኃይላቸውን ያረባረቡ ኢትዮጵያውያን ድኅረ-ጣልያን ወረራ ከወሰዷቸው ታላላቅ እርምጃዎች መኻል ኤርትራ ከእናት አገሯ መልሳ እንድትቀላቀልና አገሪቱ በባዕዳን ተፅዕኖ ለረጅም ጊዜ ያጣችውን የባሕር በር ባለቤትነት መብት ማስመለስ መቻላቸው ነበር፡፡ ያንን የዘመናት ጥረት ነው እንግዲኽ የአሁኑ ገዥዎች ከመቅጽበትና እንደዋዛ ብኩን ያደረጉት፣ በአክራሪዎችና በሌሎች አሉታዊ ኃይሎች

እየተናወጠ ባለ አካባቢ የምትገኘውን አገራችን ለአስተማማኝ ፀጥታ፣ ሰላምና መረጋጋጥ እጦት ያመቻቹትና ሕዝባችንም ቀጣይነት ለሚኖረው ብልፅግናና እድገት ያለውን ሕልም ለጊዜውም ቢሆን ያከሰሙት::

እንደሚታወቀው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከሸዓብያ መንግሥት ጋር ወዳጅነቱ ሲያከትም እና በተለይም እራሱ ሸዓብያ በተነኮሰው ጦርነት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ-አንድ ሰው ተነስቶ እብሪተኛውን የሸዓብያ ወራሪ አይቀጡ-ቅጣት ቀጥቶ ድባቅ በመታበትና አዋራጅ ሽንፈትን ባከናነበበት ወቅት ይኸው አንገብጋቢ የወደብ ጉዳይ መነሣቱና ቢያንስ አሰብን ማስመለሻ አመቺውና ሁለንተናዊ ሕጋዊና ታሪካዊ መሠረት ያለው፣ ብዙም ሊያስጠይቅ የማይችል ሥነ-ምክንያትና በአካሄድም ተቀባይነት ያለው ሁኔታ ሲፈጠር የሕወሓት/ ኢሕአዴግ ቁንጮዎች መደንገጣቸው ግልጥ ነበር:: ድንጋጤው ያንን ማድረግ የማይቻል ስለ-ሆነ ሣይሆን አገሪቱን የባሕር-በር ባለቤት የመሆን አንጡራ መብቷን ካለመገንዘብ ቢያንስ ግን ፍላጎቱ ጨርሶ ስለ-ሌላቸው ነው:: ያንን "ታሪካዊ አጋጣሚ" ላለመጠቀምና ኢትዮጵያ የራሷ ወደብ ባለቤት እንዳትሆን ለመገርገራቸው በምክንያትነት የቀረቡ አዲስ ዙር የማሣመኛ ነጥቦች ደግሞ አንድም "ኢትዮጵያ እንደዚያ ዓይነት እርምጃ ብትወስድ በዓለም ፊት እንደ ወራሪ እንድትታይ ያደርጋል፣ ... የምንጠቀምበት የወደብ ችግር የለብንም፤ ጅቡቲን፣ በርበራን፣ ሞምባሣን፣ ፖርት-ሱዳንን መጠቀም እንችላለን..." የሚል ዓይንኽን አሣየኝ ሲሉት እግርን እንደማሣየት የሚቆጠር የአልተገናኝቶም አቀራረብ ነበር የሚሰነዘረው::

**የወደብ ባለቤትነት ለምን?**

አገር-ወዳድ የኢትዮጵያውያን የባሕር-በር አስፈላጊነትን የሚያዩት የሕወሓት/ ኢሕአዴግ መሪዎች በሚያዩበት ከሸቀጥ ማስተላለፊያነት ያላለፈ ቀጭን አስተሣሰብ ላይ በተመሠረተ እይታና እምነት አይደለም:: **የቆየ ታሪካቸውን፣ ያሉበትን አስቸጋሪና ፈታኝ አካባቢያዊና ዓለም-አቀፍ ሁኔታዎችን እንዲሁም ከውጭ ለሚሰነዘር ጥቃትና ቀጥተኛና የእጅ-አዙር የባዕዳን ጫና መጋለጥን፣ ከአገራቸው አንድነት፣ ከአስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት፣ ከምጣኔ ሃብት እድገትና ብልፅግና እንዲሁም ከወደፊት ትውልዶች ዘለቄታዊ ጥቅም አኳያ ዙሪያ ጥምጥሙን በማየትና በማገናዘብ ነው::**

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ምናልባት የባሕር በር አስፈላጊነትን የሚያዩት ልክ እንደ-መሬት ፖሊሲያቸው ከጊዚያዊ መገልገያነት ውጭ አይደለም:: ስለ-ሆነም ያልተገነዘቡት አሁን "ልንገለገልባቸው እንችላለን" ከሚሏቸው ወደቦች ልክ እነሱ ማንንም ደስ ካላልቸው ወይም ለነሱ ድጋፍ የነሣን ገበሬ በማንኛውም ጊዜ ከማሣው መንቀል እንደሚችሉት ሁሉ የተባሉት ወደቦች ባለቤቶችም እነሱን በሰበብ-አስባቡና እንደፈለጉ በወደቦቹ እንዳይገለገሉ ማድረግ እንደሚችሉ ነው::

የሆነ-ሆኖ የዚኽ ጽሑፍ ዓላማ የባሕር በር በንግድ ልውውጥና በኤኮኖሚው ረገድ ስለሚኖረው አስፈላጊነትና ጠቀሜታ አይደለም:: ያንን በሙያው ለሰለጠኑ ወገኖች መተዉ ተገቢ ይሆናል::

የኢትዮጵያ አስተማማኝ አገራዊ አንድነት፣ ሰላም፣ መረጋጋት፣ ብልፅግናና እድገት አገራችን በቀይ ባሕር ላይ ከሚኖራት የባለቤትነት ቁጥጥር ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማየት ቢያንስ ባለፉት ሁለት-ሽህ ዓመታት ያሣለፍናቸውን ሂደቶችና ክስተቶች መቃኘቱ ተገቢ ይሆናል::

የአክሱም ሥልጣኔ እየተባለ የሚጠራው ገናና ዘመን ኢትዮጵያ የራሷን የንግድና የጦር መርከቦች በቀይ ባሕር ብቻ ሣይሆን ከዚያ በጣም እርቀው ሕንድ ውቅያኖስንና ሌሎችንም ጭምር በስፋት የናኙበት፣ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ከኢየሩሳሌም እስከ ሕንድ በየትኛውም የሄዱበት ቦታ ሁሉ ተከብረው ጥሪት ያፈሩት፣ ኢትዮጵያም ከራሷ አልፋ ለተጨቆኑና ሕይዎታቸው አደጋ ላይ ለወደቀ አረቦች በአንድ ጊዜ ሰላሣ ሽህ እና ሰባ-ሽህ ሠራዊት በራሷ መቶ-ሰባ የጦር መርከቦች  አሣፍራ በመላክ መታደግ የቻለችው፣ በአገር ውስጥ ጥበብ እንዲያድግ፣ የራሣችን የሆኑ የአስተዳደር ሥርዓቶች እንዲበለጽጉ ማድረግ የተቻለው፣ አንድነቷ ታፍሮና ተከብሮ፣ ዝናዋ በየትኛውም ዓለም የናኘው፣ ለተበደሉና

እንክብካቤ ለፈለጉ የውጭ ዜጎች መጠጊያ፣ ሠርተው ኑሮአቸውን ለማሻሻል የሚሰደዱባት አገር መሆን የቻለችው ተፈጥሮ የለገሳትን የቀይ ባሕር ወደቦች <u>በባለቤትነት መቆጣጠር</u> በመቻሏ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ወደቦች ላይ ያላትን የባለቤትነት ይዞታ ጥቅምና ጉዳት ይበልጥ የተገነዘቡት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሣይሆኑ እንዲያውም ባዕዳን ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ስለ-ሆነም በተለይ የፋርስና የኦቶማን ኃይሎች እየጎለበቱና እያየሉ ሲመጡ ኢትዮጵያ በሰሜንም ሆነ በምሥራቅ በተለይም በቀይ ባሕር ወደቦች ላይ ያላትን <u>ቀጥተኛ የባለቤትነት</u> ይዞታ ስታጣና በር ጠባቂና የተፈጥሮ ድንበር አስከባሪ የነበሩት የጦር መርከቦች ሲጠፉ፣ ዳሩ መኻል እየሆነ ለባዕዳን ቀጥተኛ ጥቃት እየተጋለጠች እነኝሁ ባዕዳን ተንፏቀው ተንፏቀው ውስጥ ድረስ ዘልቀው በመግባት አንድነቷ ተናግቶ፣ አገር-በቀል ሥልጣኔዋ እንዲንኮታኮት ተደርጎ፣ የሕዝቧ ባህሎች ተበውዘው፣ በዓለም የተከበሩ ኩሩ ዜጎቿ ለአስከፊ የባሪያ ንግድ ሰለባ ሆነው፣ ለድህነት የተዳረገ ሕዝቧም አንድነቱንና ትሥሥሩን እንዲያጣ ተደርጎ የውጭ ባዕዳን ኃይሎችን ብቻ ለጠቀመ ጎሣንና ሐይማኖትን መሠረት ላደረገ ዘግናኝ የርስ-በርስ እልቂት እንዲዳረግ ሆኗል፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ አንድነትና የሕዝብ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ላይ ከሦስት አቅጣጫዎች - ማለትም በሰሜን ከቀይ ባሕር፣ ከምዕራብ ዓባይን ተከትሎ እና ከምሥራቅ አሁን ሶማሌ ተብሎ ከሚጠራው በኩል፣ ተደጋጋሚ ችግሮችና ፈተናዎች ሲደርሱ ኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያ በአጠቃላይ በምሥራቅም ሆነ በሰሜን በነበሯት የባሕር በሮች፣ በተለይም በቀይ ባሕር ወደቦቿ ላይ የባለቤትነት ሉዓላዊ ቁጥጥሯን በማጣቷ ምክንያት አገራችን በቆዳ ስፋት መኮስመን ብቻ ሣይሆን ከቀረው ዓለም ተቋርጣና ሥልጣኔዋና እድገቷ ከመጨናገፍም አልፎ በአብዛኛው ደብዛው እንዲጠፋ ማድረጉን፣ ነፃነቷም ለማያባራ ፈተና መዳረጉን፣ በአገሪቱ አንድነትና በሕዝቧ ሰላም ላይም ያስከተለውን ጉዳት በደንብ የተገነዘቡ ታላላቅ የአገሪቱ መሪዎች ቅድሚያ የሰጡትና ከፍተኛ ጥረት ያደረጉበት ጉዳይ ነበር፡፡

በዚኽም መሠረት በነዚኽ አገር-ወዳድና ብሔራዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው መሪዎች/ነገሥታት ዘንድ ባዕዳንን ከጠረፍ ጠራርጎ ማስወጣትና የአገሪቱን የባሕር በር ባለቤትነት ማረጋገጡ ለአገሪቱ አንድነትም ሆነ ለውስጥ ሰላምና መረጋጋት ቁልፍ በመሆኑ ጦር አስከትተው ማዝመት አማራጭ ያልነበረው የጎለውናና የሰብዓዊ ክብር ተልዕኮ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ስለ-ሆነም አፄ አምደ-ፅዮን (1305 - 1334 )፣ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ (1426 - 1460)፣ አፄ ሰርፀ-ድንግል (1555 - 1589) በየዘመነ-መንግሥታቸው ተደጋጋሚ ጦርነቶችን በማድረግ ተስፋፊ አረቦችንና የኦቶማን ቱርክ ዘማችና ወራሪ ሠፋሪዎች ድባቅ እየመቱ የቀይ ባሕር ወደቦችን አልፎም እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፎች ከምፅዋ እከ ዘይላና ሞቃዲሾ ካሉት ቦታዎች ጠራርጎ በማስወጣት ኢትዮጵያ እንድትታፈርና ሕዝቧም በገዛ አገሩ በባዕዳን ከሚደርስበት ውርደት፣ በደል፣ ግፍና ስቃይ እፎይታን እንዲያገኝ፣ የውስጥ አንፃራዊ የሰላም አየርን በኩራት እንዲተነፍስ አስችለዋል፡፡ ይኽ በሆነ ቁጥር ኢትዮጵያውያን ጥሬ ሃብታቸውና ጥሪታቸው በባዕዳን ከመዘረፍ ተርፎ፣ ሥነ-ልቦናዊ ኩራት የተላበሱበት ብቻ ሣይሆን ቁሣዊ መሻሻልን ያዩበት፣ ከውጭው ዓለም ጋርም ግንኙነት በመመሥረት ገርገጭ ብሎ የቆመው ሥልጣኔ መልሶ እንዲንቀሣቀስ ዕድል የሰጠ ሁኔታን አስገኝቷል፡፡ ያ መሆን የቻለው ከሐማሴን እስከ ትግራይ፣ ከአንጎት እስከ ባሌ፣ ከጎንደር እስከ እናርያ፣ ወዘተ ያለው ኢትዮጵያዊ አርሶ-አደር የራሱን ስንቅ ሰንቆ፣ ቤተሰቡን ትቶ፣ በባዶ እግሩ ባደረገው ወደር-የለሽ መስዋዕትነት መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም፡፡

ኢትዮጵያ በቀይ ባር ወደቦች ላይ **የባለቤትነት ቀጥተኛ ቁጥጥር** በማጣቷ ምክንያት ባዕዳን ተንፏቀው ተንፏቀው ምድረ-ባኅር/ሪ በመባል ይታወቅ የነበረውን የሰሜኑን የአገሪቱ ክፍል በመጀመሪያ ኦቶማን ቱርኮች፣ ከዚያ ግብፆችና በመጨረሻም ጣሊያኖች ወርረው በመያዝ ኤርትራ የሚል አዲስ ስም በመስጠት ከቀረው ኢትዮጵያ ነጥለው በወራሪ ቅኝ-ገዢነት ሥር አቆይተውታል፡፡ እነኝኽ ባዕዳን በያዙት ይዞታ ሣይቆጠቡ በቀረው ኢትዮጵያ ከዚያም ደቡብ ባሉ የአፍሪቃ አገሮች ላይ የነበራቸውን የመስፋፋት ዓላማ እውን ማድረግ የሚችሉት ኢትዮጵያን መውጫ-መግቢያ የባሕር በር ማሣጣት እንደ-ሆነ አላጡትም፡፡

***በክፍል ሁለት ይቀጥላል ...***